301

*Updated-Second Draft*

# በኢትዮጵያ የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓትን ለማቋቋም የተዘጋጀ የዕቅድና አፈፃፀም ስልት ረቂቅ

## *ክፍል 1 - በወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ሥርዓት ላይ ያተኮረ*

ቫይታል ስታትስቲክስ
ምዝገባ ጥናትና ምርምር
መምሪያ - ማስባ
ህዳር 1994

*Updated-Second Draft*

# በኢትዮጵያ የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓትን ለማቋቋም የተዘጋጀ የዕቅድና አፈፃፀም ስልት ረቂቅ

## *ክፍል 1 - በወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ሥርዓት ላይ ያተኮረ*

ቫይታል ስታትስቲክስ
ምዝገባ ጥናትና ምርምር
*መምሪያ - ማስባ*
ህዳር 1994

# ማውጫ


| ተ.ቁ | ርዕስ | ገጽ |
|---|---|---|
| 1. | አጠቃላይ | 1 |
| 2. | አስፈላጊነት | 4 |
| 3. | በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነቶች(ቫይታል) ስታትስቲክስ መረጃ አሰባሰብ | 6 |
| 4. | በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለሥልጣን የቫይታል (ወሳኝ ኩነቶች) ስታትስቲክስ የሥራ ክፍል አደረጃጀት | 8 |
| 5. | የምዝገባና የስታትስቲክስ ሥርዓቶች ማቋቋም የተግባር ዘርፎችና የአፈጻጸም ስልት | 10 |
| 6. | ተጓዳኝ የጥናትና ምርምር የዝግጅት ተግባራት | 19 |
| | አባሪ ሀ | 22 |
| | አባሪ ለ | 23 |
| | አባሪ ሐ | 26 |

# በኢትዮጵያ የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓትን ለማቋቋም የተዘጋጀ የዕቅድና አፈፃፀም ስልት ረቂቅ

## ክፍል 1 - በወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ሥርዓት ላይ ያተኮረ

### 1. አጠቃላይ

በስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ አልፎም በስታትስቲክስ መረጃ አቅርቦት ዘርፍ ሶስት መሠረታዊ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ወይም መንገዶች ይታወቃሉ። እነርሱም የቆጠራ መንገድ (Enumeration Method)፣ የምዝገባ መንገድ (Registration Method) እና የአስተዳደር መንገድ (Administrative Method) በመባል ተለይተዋል (UN, 1955 (5))። በስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ መረጃ አቅርቦት በቆጠራ መንገድ የሚካተቱ የስታትስቲክስ ያጠናን ዘዴዎች የሕዝብና ቤት ቆጠራዎች (Population and Housing Censuses) እና የስነ-ህዝብ ናሙና ጥናት (Demographic Sample Survey) ሲሆኑ በምዝገባ መንገድ የሚካተቱት ደግሞ የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ[1] (Civil Registration and Vital Statistics) እና የሕዝብ ምዝገባ (Population Register) ናቸው። የአስተዳደር መንገድ ከአስተዳደር መዛግብት (Administrrative Records) የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴን ያቀፈ ሲሆን በአመዛኙ በደጋፊነት (Supplementary) የሚያገለግሉ የስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ መረጃዎች የሚገኙበት ነው። በስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ ዘርፍ ዋነኞቹ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች ቆጠራ፣ የስነ-ህዝብ ናሙና ጥናት፣ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ሥርዓት እና የሕዝብ ምዝገባ የተሰኙት ናቸው። ከላይ የተጠቀሱት የስታትስቲክስ መረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች በአፈጣጠራቸው፣ በሚያቀርቡት መረጃ ዓይነትና በአጠቃቀማቸው ልዩነትና አንድነት አላቸው። መጠነኛ ግንዛቤ ለመስጠት ያህል እያንዳንዳቸውን ከታች በአጭሩ እንመለከታለን።

#### 1.1 ቆጠራ (Census):-

በህዝብና ህዝብ-ነክ ስታትስቲክስ ጥናት ሁለት የአጠቃላይ ቆጠራ መረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች አሉ። እነርሱም የሕዝብ ቆጠራ እና የቤቶች ቆጠራ በመባል ይታወቃሉ። ምንም እንኳን ሁለቱ ቆጠራዎች ማለትም የሕዝብና የቤት ቆጠራዎች በተናጠል የመካሄድ ልምድ ቢኖራቸውም (UN 1958 መጽሄትን

[1] ሁለት የመረጃ ስርዓቶችን ማለትም የሕዝብ የክብር መዝገብ ምዝገባ ሥርዓት እና የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ሥርዓትን ያካተተ ነው።

ይመልከቱ) በአሁኑ በደረስንበት ዘመን የሕዝብና የቤት ቆጠራዎችን አብሮ ማካሄዱ የተመረጠና በተባበሩት መንግስታትም የሚደገፍ አሠራር ነው። በስታትስቲክስ መረጃ መሰብሰብ አሠራርና ታሪክ የሕዝብ ቆጠራ በዓለማችን ረጅም ዕድሜ ያስቆጠረ የስታትስቲክስ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው። ለምሳሌ እንደ አሜሪካ የመሳሰሉ ሀገሮች ከ18ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ አንስቶ የሕዝብ ቆጠራን በዘመናዊ አሠራሩ ሲያካሂዱ ቆይተዋል። በሌላ በኩል እንደ ኢትዮጵያ በመሰሉ ሀገሮች ደግሞ ይኸ የህዝብ ቆጠራ ተግባር የቅርብ ጊዜ ክስተት ነው። በመሆኑም በኢትዮጵያ እስካሁን ሁለት የሕዝብና ቤት ቆጠራዎች ብቻ ተካሂደዋል።

የሕዝብና ቤት ቆጠራ በዓለም ላይ በቆየባቸው ዘመናት በዓላማው፣ በቴክኒካዊ አሠራሩና በአጠቃቀሙ መሠረታዊ ለውጦችንና ዕድገቶችን አሳይቷል። በጥንቱ ዘመን የሕዝብ ቆጠራ የሚካሄድበት ዋነኛ መነሾ የአንድን ሀገር የወታደር አቅምን ለማወቅ፣ ግብር ከፋዩን እና ለሥራ የደረሰውን የህዝብ ቁጥር ለመለየት ነበር። በመንግስት አስተዳደር ውስጥ የሕዝብን ተሳትፎ የሚያካትት ፖለቲካዊ አሠራሮች እየሰፉ በሄዱ ቁጥር በህዝባዊ ምርጫ የሚወከሉ የሕዝብ ተመራጮችን የመምረጡ ስርዓት በህዝብ ቆጠራ መረጃ ላይ እንዲመሠረት ተደርጓል። ከአሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ጀምሮ የሕዝብ ቆጠራ የመረጃ ፍላጎት እየሰፋ መጥቶ የቆጠራ መጠይቆች ይዘት በስነ-ህዝብ መረጃዎች ማለትም የወሊድ፣ የሞት፣ የሥራ ሥምሪት፣ የፍልሰትና መሰል የግለሰቦች የስነ-ህዝብ ባህርያትን እንዲያካትቱ ከመደረጉም ባሻገር ዘመናዊ የአቆጣጠር ሥርዓት ሊይዝ ችሏል። ባለንበት ዘመን ከሕዝብና ቤት ቆጠራ የሚገኙ መረጃዎች የአንድን ሀገር የፖለቲካ ሥርዓት አደረጃጀት፣ የሕዝብ አስተዳደር እና የበርካታ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ግልጋሎት የመስጠት ተግባራት ዕቅድ ዝግጅትና አፈፃፀም መሠረት በመሆን እያገለገሉ ይገኛሉ።

## 1.2 <u>የስነ-ህዝብ ናሙና ጥናት</u> (Demographic Sample Survey):-

የሕዝብና ቤት ቆጠራ በየተወሰኑ ዓመታት (በአመዛኙ የዓለም ክፍል በየ10 ዓመት) የሚካሄድ የስታትስቲክስ መረጃ መሰብሰብ ተግባር ነው። በአንፃሩ የስነ-ህዝብ ናሙና ጥናቶች በቆጠራዎች መሃከል የሚከሰቱ ለውጦችን ለመከታተልና በቆጠራዎች ሊሸፈኑ ወይም በጥልቀት ሊሰበሰቡ ያልቻሉ የመረጃ ዘርፎችን ለመሰብሰብ በናሙና በተመረጡ ናሙናዎች ላይ የሚካሄዱ ጥናቶች ናቸው።

በስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ መስክ የሚካሄዱ ናሙና ጥናቶች ዓይነት በርካታ ነው። እንደየሀገሩ የመረጃ ፍላጎት፣ የአቅርቦት መጠንና የዕድገት ደረጃ የናሙና ጥናቶች ዓይነትና ብዛት ይለያያል። በጥቅሉ የስነ-ህዝብ ናሙና ጥናት ሙሉ

ለሙሉ ለስነ-ህዝባዊ፣ ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕቅድ ዝግጅት እና የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ የሚያስፈልጉ የስታትስቲክስ መረጃዎች ማስገኛ ዘዴ ነው።

1.3 <u>ወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ሥርዓት</u> (Vital Statistics System):-

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና የፍቺ ምዝገባን በዋነኝነት ለህግ፣ ለአስተዳደርና ለስታትስቲክስ የሚያስገኙትን ግልጋሎት መሠረት በማድረግ ሁለት የመረጃ አሰባሰብ ተግባራትን (Functions) ለይቶ የሚካሄድ የመረጃ አሰባሰብ ሥርዓት ነው። እነዚህም ተግባራት የምዝገባ ተግባር (Registration Function) እና የስታትስቲክስ ተግባር (Statistical Function) በመባል ይታወቃሉ። እነዚህንም ተግባራት መሠረት ያደረጉ የመረጃ አጠንቃቀር የአሠራር ሥርዓቶች ተበጅተዋል። እነርሱም የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት (Civil Registration System) እና የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ሥርዓት (Vital Statistics System) በመባል ይታወቃሉ።

በምዝገባው ተግባር የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች አመዘጋገብ ሥርዓትን በመከተል ግለሰባዊ ኩነቶች ለህግ፣ ለስታትስቲክስና ለአስተተዳደር የመረጃ ፍላጎት በሚያሙዋሉበት ቴክኒካዊ የአመዘጋገብ ዘዴ በተዘጋጁ መዝገቦች ላይ እንዲመዘገቡ ይደረጋል። የሕዝብ የክብር መዝገብ አመዘጋገብ ሥርዓትን ተከትለው የተመዘገቡ ወሳኝ ኩነቶች ለስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ የመረጃ ፍላጎት ሊያሙዋሉ በሚችሉበት አኳኋን በመጠይቆችና ቅጾች ይሰበሰባሉ፣ ይጠናቀራሉ፣ ከዚያም ለተጠቃሚ ይሠራጫሉ። ይኸም ተግባር የሚጠቃለለው በወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ሥርዓት ነው። በመሆኑም የሕዝብ የክብር መዝገብ ምዝገባ ግላዊ ወሳኝ ኩነቶችን ለህግ፣ ለስታትስቲክስና ለአስተዳደር ግልጋሎት በቀጣይነትና በቋሚነት በህግ አስገዳጅነት የመመዝገብ፣ የማከማቸትና ለግለሰቦች ህጋዊ የምስክር ወረቀቶችን የመስጠት ተግባርን የሚያጠቃልል ሲሆን በአንፃሩ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ደግሞ ከሕዝብ የክብር መዝገቦች ላይ ግለሰባዊ ወሳኝ ኩነቶች መረጃን በመሰብሰብ፣ በማጠናቀርና በመተንተን በተለያየ የአስተዳደር ዕርከን ደረጃ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻ እና የፍቺ ስታትስቲክስ መረጃዎችን በቀጣይነትና በቋሚነት የማጠናቀርና የማሠራጨት ተግባራትን ያጠቃልላል።

በኢትዮጵያ እንደተቀሩት በርካታ ታዳጊ ሀገሮች ሁሉ የሕዝብ የክብር መዝገብ ምዝገባና የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ሥርዓቶች አልተመሠረቱም። በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ ምናልባትም ከሌሎች ታዳጊ ሀገሮች የሚለዩዋት ሥርዓቶቹን ለመመሥረት ሀገር አቀፍ ሙከራ እስካሁን አለማድረጓ ጭምር ነው።

### 1.4 **<u>የሕዝብ ምዝገባ</u> (Population Register)**

በዓለማችን በቁጥር ከሚጠቀሱ ጥቂት በኢኮኖሚ የበለፀጉ ሀገሮች በስተቀር የሕዝብ ምዝገባ አሰራር በተሟላ አኳኋን በሥራ ላይ አልዋለም:: በመሠረቱ ሕዝብ ምዝገባ ዋነኛ አገልግሎቱ ለአስተዳደርና ለስታትስቲክስ ተግባር የሚውሉ ግለሰባዊ መረጃዎችን በቀጣይነትና በቋሚነት መመዝገብ ነው:: በርግጥ የሕዝብ ምዝገባ በአንድ ሀገር በተሟላ መልኩ ካደገ በየወቅቱ የሚካሄድን የህዝብ ቆጠራ ሊተካ ይችላል::

## 2. <u>አስፈላጊነት</u>

በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ሥርዓትን የማቋቋም አስፈላጊነትን ለመረዳት ከሥርዓቱ የሚገኙ የኩነቶች መረጃዎች ከሚሰጡት ግልጋሎት አንፃር መመልከቱ ጠቃሚ ይሆናል:: ለፖለቲካዊ አስተዳደር አደረጃጀት፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎችን፣ ዕቅዶችንና ፕሮግራሞችን ለማዘጋጀት እንዲሁም የእነዚህን ፖሊሲዎች፣ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች አፈፃፀምና የአፈፃፀም ግምገማ ለማድረግ በግብዓትነት የሚፈለጉ የስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ መረጃዎች በአግባባዊና በተለመዱ (Conventional and Traditional) ሁለት መንገዶች ይሰበሰባሉ:: በአንድ ወገን አንድ ወቅትን የተመለከቱ የህዝብ ብዛትና ባህርያትን የሚያመለክቱ መረጃዎች በሕዝብና ቤት ቆጠራና ቆጠራ መሰል ናሙና ጥናቶች በቆጠራ መንገድ የሚሰበሰቡ ሲሆን በሌላ ወገን ደግሞ የህዝብ ብዛት ዕድገትን የሚወስኑ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃዎች በቀጣይነትና በቋሚነት በወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ሥርዓት አማካይነት በምዝገባ መንገድ ይሰበሰባሉ:: እነዚህም መረጃዎች በተለይም ከመንግስት አስተዳደር አንፃር ለህዝባዊ ምርጫ፣ የፌደራል መንግስትን የበጀት ድልድል ለማድረግ፣ ለትምህርት፣ ለጤናና ተመሳሳይ የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዕቅዶች ዝግጅት፣ አፈፃፀምና የአፈፃፀም ግምገማ ለማድረግ በሀገር፣ በክልል አልፎም በትንሹ የአስተዳደር ዕርከን ደረጃ በቀጣይነትና በቋሚነት ይፈለጋሉ:: ለተጠቀሱት ማህበረሰባዊ የተግባር ዘርፎች የሚፈለጉትን መረጃዎች በጥራትና ወቅታዊነታቸውን በመጠበቅ ለማስገኘት የየወቅቱን የህዝብ ብዛት (stock) እና ቀጣይ ለውጦችን የሚከታተሉ (Flow) የመረጃ አሰባሰብ ስርዓቶችን በማጣመር መረጃዎችን መሰብሰብ ይጠይቃል::

የሕዝብ ብዛት መረጃ ከሕዝብና ቤት ቆጠራ የሚገኝ ሲሆን ይኸን መረጃ ወቅታዊ ለማድረግ በዋነኛነት የየዓመቱን የህዝብ ብዛት ዕድገት ምጥንነትን የሚያመለክቱ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ምጣኔዎች ቀጣይና ቋሚ ከሆነ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ሥርዓት መገኘት አለባቸው:: በሌላ አገላለጽ የህዝብ ብዛት ዕድገት ስሌትን በወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ላይ ተመስርቶ በቀጣይነትና በቋሚነት እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር ዕርከን ለማግኘት ከወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የሚሰበሰቡ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃዎች መገኘት ይኖርባቸዋል:: እንደሚታወቀው የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃ በቀጣይነትና በቋሚነት

የሚገኘው ከሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓት ነው። በጥቅሉ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃዎች አስፈላጊነት ከታች በተመለከቱት በዋነኛ የመረጃ ዓይነቶችና ግልጋሎቶች ላይ ይመሠረታል።

2.1 ዓመታዊ የሕዝብ ብዛት ዕድገት ስሌትን፣ የጤና ግልጋሎት አቅርቦትና የጤና ደረጃ ግምገማ ለማድረግ ግብዓት የሚሆኑትን ወቅታዊና ትክክለኛ የወሊድ እና የሞት ምጣኔዎችን በሀገር አቀፍ፣ በክልልና አነስተኛ የአስተዳደር ዕርከኖች በቀጣይነትና በቋሚነት ለማስገኘት፣

2.2 ወቅታዊና ትክክለኛ የሕዝብ ብዛት መረጃን በየዓመቱ እስከ ትንሹ የአስተዳደር ዕርከን/ ደረጃ በቀጣይነትና በቋሚነት ለማስገኘት፣

2.3 ወቅታዊና ትክክለኛ የሞት ምክንያት መረጃን እስከ ትንሹ የአስተዳደር ዕርከን/ ደረጃ በቀጣይነትና በቋሚነት ለማስገኘት፣

2.4 በፖለቲካዊና የሕዝብ አስተዳደር አደረጃጀት ዘርፍ ወቅታዊና ትክክለኛ የስነ-ህዝብ ስታቲስቲክስ መረጃ ለማስገኘት፣ ይኸም ማለት፦

ሀ. የሕዝባዊ ምርጫን በማስፈፀም የዕቅድ ዝግጅቶችን ለማድረግ በተለይም የምርጫ ጣቢያዎችን ለመከለልና ብዛታቸውን ለመወሰን ወቅታዊና ትክክለኛ የስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ መረጃ በቀጣይነት እስከ ትንሹ የአስተዳደር ዕርከን ለማስገኘት፣

ለ. የፌደራል መንግስቱን በጀት ለክልል መንግስታት እና የተዋረድ አስተዳደሮች ለማከፋፈል ለሚዘጋጀው ቀመር ወቅታዊና ትክክለኛ የስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ የመረጃ ግብዓት ለማስገኘት፣

ሐ. የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የመቀመጫ ክፍፍልን ለመደልደል ወይም ለማደስ የሚያስችል ወቅታዊና ትክክለኛ የስነ-ህዝብ ስታቲስቲክስ የመረጃ ግብዓት ለማስገኘት፣

2.5 ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የግልጋሎትና የልማት ሥራዎች ፖሊሲና ዕቅድ ዝግጅት እንዲሁም የአፈፃፀም ግምገማ እስከ ትንሹ የአስተዳደር እርከን ለማድረግ የስነ-ህዝብ ስታቲስቲክስ መረጃ ግብዓት በቀጣይነትና በቋሚነት ለማስገኘት፣

ይኸም ማለት፦

ሀ. የጤናና የትምህርት ፍላጎቶችንና ግልጋሎቶችን (የተቋማትን ግንባታ ጨምሮ) እስከ ትንሹ የአስተዳደር ዕርከን ለማቀድ እንዲሁም ግልጋሎቱን ለመስጠትና አሰጣጡን ለመገምገም በቀጣይነትና በቋሚነት ወቅታዊና ትክክለኛ የስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ የመረጃ ግብዓት ለማስገኘት፣

ለ. የሞት ምክንያት (Cause of death) መረጃን መሠረት በማድረግ ዝርዝር ሀገራዊ የበሽታዎች ምደባ (Detailed National Cause of Death Classification) በማዘጋጀት ስለ በሽታዎች ስርጭትና ክትትል ጥናትና ምርምር እስከ ትንሹ የአስተዳደር ዕርከን/ ደረጃ ለማድረግ፣

ሐ. የምርቶችንና የአገልግሎቶችን አቅርቦት እስከ ትንሹ የአስተዳደር ዕርከን ደረጃ በዕቅድ (ፍላጎትንና አቅርቦትን በማመጣጠን) ላይ ተመስርቶ ለማምረትና ለማቅረብ የሚያስችል ወቅታዊና ትክክለኛ የስነ-ህዝብ ስታቲስቲክስ መረጃ ለማቅረብ፣

መ. የቤተሰብ ደህንነትን (Family Welfare) ለመጠበቅና ለመንከባከብ የሚያስችል ዝርዝር ቤተሰባዊ መረጃዎችን እስከ ትንሹ የአስተዳደር ዕርከን ደረጃ ቀጣይና ቋሚ የሥነ-ሕዝብ ስታትስቲክስ መረጃ ለማቅረብ፣

ሠ. የሕዝብ እስፋፈርንና መከተምን በሥርዓት ለማደራጀት፣ የመሠረተ ልማት አውታሮችን እስከ ትንሹ የአስተዳደር ዕርከን በዕቅድ ለመዘርጋትና ቀጣይና ቋሚ ክትትል ለማድረግ ግብዓት የሚሆኑ የስነ-ህዝብ ስታቲስቲክስ መረጃዎችን በቀጣይነትና በቋሚነት ለማቅረብ፣

## 3. በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነቶች (ቫይታል) ስታትስቲክስ መረጃ አሰባሰብ

እንደሚታወቀው በኢትዮጵያ የመደበኛ ስታትስቲክስ (Designated Statistics) መረጃን የመሰብሰብ ተግባር ከተጀመረ በጠቅላላ አራት አስርት ዓመታትን አስቆጥሯል:: ከዚህም ጊዜያት ውስጥ በዓይነቱና በይዘቱ ሰፋት ያለው የስታትስቲክስ መረጃ የመሰብሰብ ተግባር መከናወን የጀመረው ከ1972 ዓ.ም ወዲህ ነው:: በስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ መስክ ከ1976 ዓ.ም ቀደም ሲል የነበሩ የመረጃ ምንጮች በናሙና ጥናቶች ላይ የተመሠረቱ ነበሩ:: በ1976 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ የተካሄደው ሀገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ የሀገሪቱን የሕዝብ ብዛትና የዕድገት ምጣኔዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ሊያስገኝ ችሏል:: በዚህ ቆጠራ በቆጠራው

ዓመት የሀገሪቱን የሕዝብ ብዛትና ምጣኔ እንዲሁም ልዩ ልዩ የስነ-ህዝብ ባህርያት መረጃዎች ሊገኙ ችለዋል። ከዚህም በተጨማሪ የቤቶችን ብዛትና ሁኔታ የሚያመለክት መረጃ አስገኝቷል። በተመሳሳይ ሁለተኛው የሕዝብና ቤት ቆጠራ በ1987 ዓ.ም በመላ ሀገሪቱ ተካሂዷል።

የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓትን ባልዘረጉ ሀገሮች የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃዎች በዋነኛነት የሚገኙት ከሕዝብ ቆጠራ ነው። ከዚህም በተጨማሪ በቆጠራዎች መሃከል የሚካሄዱ ናሙና ጥናቶች የቆጠራ መረጃ አሰባሰብ ስልትን በመከተል የወሳኝ ኩነት ስታትስቲክስ መረጃዎችን ናሙና ጥናቱ ለተካሄደበት ዓመት ያስገኛሉ። በመሠረቱ ቆጠራዎችም ሆኑ ናሙና ጥናቶች በቀጣይነትና በቋሚነት የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃዎችን የማያስገኙ ከመሆናቸውም በላይ ለቆጠራው ዓመት እንኳ በጥራቱ የተሟላ የወሳኝ ኩነት መረጃ ማስገኘት እንደማይችሉ በበርካታ ሀገሮች የተደረጉ ሙከራዎች አሳይተዋል። በዚህ ረገድ አሜሪካ በህዝብ ቆጠራ አማካይነት በተለይም የሞት ምጣኔ መረጃ ለማግኘት ሙከራ ካደረጉ ሀገሮች አንዷ እና በግንባር ቀደምትነት የምትጠቀስ ነች። በአሜሪካ በዚህ ረገድ ከተደረጉ ሙከራዎች የተገኙ ውጤቶችና የተደረሱ ድምዳሜዎች የሚከተለውን ይመስላሉ።

*"The fundamental deficiency of the census method for collecting vital statistics is that it can, at best, produce returns for the census year and no other. Census years are usually ten years apart. For the intercensal years, current vital statitics are not produced by the census method and, thus, that method fails in the first and minimum requsite for vital statistics, i.e., the production of data on a current basis. Not only does the census method fail to provide intercensal data but, as seen above, it fails also to record completly the occurrence of births and deaths even for the census year. ..." UN, 1955(6).*

እንደተቀሩት በርካታ ታዳጊ ሀገሮች ሁሉ በኢትዮጵያም የምዝገባ ስርዓቱ ያልተዘረጋ በመሆኑ የወሊድ እና የሞት ስታትስቲክስ ምጣኔ መረጃዎች ከሕዝብና ቤት ቆጠራ፣ ከአንድ ወይም ተከታታይ የስነ-ህዝብ ናሙና ጥናቶች እና የተለያዩ የአጠናን ስልቶችን ካጣመሩ የመረጃ ምንጮች ይገኛሉ። እነዚህ የመረጃ ምንጮች የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃዎችን ለወቅታዊ ፍላጎት በሚሆን አሠራር በጊዜያዊና ዘወርዋራ መንገድ መረጃ ከማስገኘት ባሻገር በቀጣይነትና በቋሚነት ወቅታዊና በጥራቱ አስተማማኝ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃ ምንጭ በመሆን ሊያገለግሉ እንደማይችሉ የታወቀ ነው።

በመሆኑም የሀገሪቱ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃ አሰባሰብ ወደ አግባባዊው (Conventional) እና ዘላቂው የመረጃ አሰባሰብ ሥርዓት ማለትም የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓት በሂደት እየተተካ መሄድ ይኖርበታል።

## 4. በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለሥልጣን የቫይታል (ወሳኝ ኩነቶች) ስታትስቲክስ የሥራ ክፍል አደረጃጀት፤

የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለሥልጣን (ቀደም ሲል የስታትስቲክስ ጠቅላይ ጽ/ቤት በመባል የሚታወቀው) ከተቋቋመ የ40 ዓመታት ዕድሜን አስቆጥሯል። የባለስልጣኑ መ/ቤት ከተቋቋመ ጀምሮ በአወቃቀሩና በአስተዳደሩ በርካታ የአደረጃጀት ለውጦችን አድርጓል። ቫይታል ስታትስቲክስ እንደ አንድ የስነ-ህዝብ የስታትስቲክስ የሥራ ዘርፍ በቡድን ደረጃ በመዋቀር ጥቂት ከፍተኛና መለስተኛ ባለሙያዎችን በመያዝ ለበርካታ አመታት በባለሥልጣኑ ሥር ተዋቅሮ ቆይቷል።

በሀገሪቱ ወደፊት የሚቋቋመውን የወሳኝ ኩነቶች (የቫይታል) ስታትስቲክስ ምዝገባ ሥርዓት በሕግ፣ በቴክኒክ፣ በአስተዳደርና በበጀት በኩል ሊገጥሙ የሚችሉ ችግሮችን በቅድሚያ ለማጥናት በሚል ዓላማ በ1969 ዓ.ም ከ10 በማይበልጡ የገጠርና የከተማ ቀበሌዎች የሙከራ ጥናት ለአንድ ዓመት በባለሥልጣኑ ተካሂዶ ነበር። ምንም እንኳ የሙከራ ጥናቱ የአጠናን መሠረት አግባባዊውን የምዝገባ ሥርዓት በማቋቋም ላይ የተመሠረተ ቢሆንም በኦፕሬሽን አደረጃጀቱና አፈፃፀሙ በቂ የጥናት ዝግጅት የተደረገበት ያልነበረ ስለነበረ ጅማሮው ውጤት ሳያስገኝ በዓመቱ ሊቋረጥ ችሏል።

በመቀጠልም በ1973 ዓ.ም «የተቀናጀ ብሄራዊ የቤተሰብ ሰርቬይ ፕሮግራም» በተጀመረበት ወቅት ቫይታል ስታትስቲክስን አስመልክቶ በተከታታይ ናሙና ጥናቶች መረጃዎችን ለመሰብሰብ በታሰበው መሠረት በ1975 ዓ.ም በሁሉም ክፍለ ሀገራት በተመረጡ 500 ገ/ማህበራት የሙከራ ጥናቱን ለማድረግ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል። ገጠርን መሠረት ባደረገው በተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም በመታቀፍ የቫይታል ስታትስቲክስ ጥናት በ1979 ዓ.ም እንዲሁም ለ10 ዓመታት ከተቋረጠ በኋላ ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ ከተሞችን የጨመረና ሁለት የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎችን ያጣመረ (Dual Records System) የአጠናን ስልትን በመከተል ለተከታታይ ሶስት ዓመታት ሙከራዎች ሲደረጉ ቆይቷል።

ምንም እንኳ የተለያዩ የአጠናን ስልቶችን በመጠቀም በተለያየ ጊዜ የሙከራ ጥናቶች ቢደረጉም፣ የተደረጉት የሙከራ ጥናቶች በአግባባዊ መንገድ የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓትን በማቋቋም ላይ በመመሥረት የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ስርዓትን ለማቋቋም የተሞከሩ አልነበሩም። በሌላም በኩል የሙከራ ጥናቶቹ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባን ድርጅታዊ አወቃቀርና አደረጃጀትን ተከትለው በቀጣይነትና በቋሚነት የምዝገባ ተግባሩን ለማከናወን ያልታቀዱ፣ ለዘለቄታው የምዝገባ ተግባሩን ማከናወን የሚገባውን መንግስታዊ ተቋምም ሆነ ተባባሪ ድርጅቶችን ያላሳተፉ ነበሩ። በተጨማሪም ምዝገባውን ቀጣይ፣ ቋሚና በሽፋኑም የተሟላ እንዲሁም ህጋዊ ለማድረግ ሁሉንም የሀገሪቱን ክፍል የሚሸፍንና የሀገሪቱን ተጓዳኝ የፍትሀ ብሄር እና የስታትስቲክስ ህጎችን መሠረት ያደረገ የምዝገባ ህግ

ለማዘጋጀትና ለመተግበር ያለመ አልነበረም። ከዚህም በላይ ዓለም አቀፍ የምዝገባ የአሠራር መርሆዎችን በመከተል የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባንና የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ሥርዓቶችን የመረጃ አሰባሰብ፣ አጠናቃቀር፣ አጠቃቀም፣ የአስፈፃሚ ተቋማቱን ህጋዊና አስተዳደራዊ አወቃቀር አስቀድሞ በጥናት ላይ ተመሥርቶ በዕቅድ ያልቀረጸና በዓላማና በአተገባበሩ በቀጣይነትና በቋሚነት ሊያገለግል በሚችል የአሠራር መመሪያ ተደግፎ የተመራ አልነበረም። በጥቅሉ ቀደም ሲል የተደረጉት ሙከራዎች የተሻሉ የቫይታል ስታትስቲክስ ምጣኔዎችን (Vital rates) በስነ-ህዝብ ስታቲስቲክስ ናሙና የአጠናን ዘዴዎች ለማግኘት ከሚደረጉ ጥረቶች የተለዩ ጥናቶች አልነበሩም። በመሆኑም በተለያዩ የዓለም ክፍሎች በዚህ መልክ የተጀመሩ የሙከራ ጥናቶች ከገጠማቸው ስኬታማ ያልሆነ ውጤት ውጭ በኢትዮጵያም የተሞከረው ሙከራ ጥናት ውጤት የተለየ ሊሆን አልቻለም። በመሆኑም በጥናቱ የሚሸፈኑ የጥናት ቦታዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ ከመጨመር ይልቅ እየቀነሱ ለመሄድ፣ በየጊዜውም ለመቋረጥ በቅተዋል።

ለባለሥልጣን መ/ቤቱ በ1989 ዓ.ም በመንግስት ፀድቆ በወጣው ድርጅታዊ መዋቅር የቫይታል ስታትስቲክስ የሥራ ክፍል በመምሪያ ደረጃ እንዲዋቀር ተደርጓል። በዚህም አወቃቀሩ ሁለት ቡድኖች እንዲኖሩት ተደርጓል። በቫይታል ስታትስቲክስ ምዝገባ ጥናትና ምርምር መምሪያ ሥር የተዋቀሩት ሁለቱ ቡድኖች አደረጃጀት የመምሪያውን የወቅቱንና የወደፊት አካሄድ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የተደራጁ ናቸው። ሁለቱ ቡድኖች የቫይታል ስታትስቲክስ ጥናትና ምርምር ቡድን እና የቫይታል ስታትስቲክስ ምዝገባ ቡድን በመባል ይታወቃሉ።

የሁለቱን ቡድኖች ልዩነትና አንድነት ለመረዳት በኢትዮጵያ የወቅቱን የቫይታል ስታትስቲክስ መረጃ ምንጮችን እና የወደፊት ፍላጎትን አጣምሮ ማየት ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ የቫይታል ስታትስቲክስ ምዝገባ ቡድን የቅርብ ጊዜ ተግባር ቀጣይ እና ቋሚ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃ ምንጭ የሆነውን የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓትን ለማቋቋም አስፈላጊ የዝግጅት ተግባሮችን በማከናወን ላይ ያተኮረ ነው። በመሆኑም የቡድኑ የወቅቱ ተግባር በሀገሪቱ የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ በቴክኒክ፣ በአስተዳደርና በህግ ረገድ ተሟልቶ የሚቋቋምበትን ቴክኒካዊ የጥናትና የምርምር ተግባር ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመተባበር ማከናወን ይሆናል። በሌላ በኩል የቫይታል ስታትስቲክስ ጥናትና ምርምር ቡድን የቅርብ ጊዜ ተግባር እየተቋቋመ ካለው የሕዝብ የክብር መዝገብ ምዝገባ ሥርዓት እና ከሌሎች የአጠናን ስልቶች ማለትም ቆጠራና ናሙና ጥናቶች የሚገኙ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃዎችን በማጠናቀር ለጥናትና ምርምር እንዲሁም ለመረጃ ተጠቃሚዎች የጥራት ደረጃቸውን በሚያመላክት አኳኋን የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃዎችን ማጠናቀርና ማስራጨት ይሆናል።

የነዚህ ሁለት ቡድኖች ተግባር በረጅሙ ጊዜ ማለትም በሀገራችን የህዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ሲዘረጋ ቀጣይና ቋሚ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃን እስከትንሹ የአስተዳደር ዕርከን ድረስ ማመንጨት ይሆናል። ይኸም ሲሆን ወደዚህ ደረጃ ለመድረስ በርካታ የዝግጅት ተግባራትን ማከናወን የሚጠይቅ ከመሆኑም ባሻገር በዚህም ሂደት በበርካታ ሀገሮች እንደታየው የቫይታል ስታትስቲክስ የሥራ ክፍል አደረጃጀት እየሰፋና ራሱን ወደቻለ መ/ቤት እያደገ የሚሄድ እንደሚሆን ይጠበቃል።

## 5. <u>የሥርዓቶቹ ማቋቋም የተግባር ዘርፎችና የአፈፃፀም ስልት</u>

የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ዕውን መሆን በዋነኝነት መንግስት ለህብረተሰቡ ለሚሰጠው ህጋዊ፣ አስተዳደራዊና ስነ-ህዝባዊ አገልግሎቶች ያደራጃቸው ግልጋሎት ሰጪ ተቋማት በትክክለኛና ወቅታዊ መረጃዎች ላይ በመመሥረት እንዲመሩና እንዲደራጁ በሚኖረው የግንዛቤ ደረጃና በዚያም ላይ ተመሥርቶ የምዝገባ አሠራሩ እንዲቋቋም በሚያሳየው ፍላጎት ላይ ይመሠረታል። ይኸም ሲሆን የምዝገባ ሥርዓቱ አቋቋም ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው ሁለት ተግባራትን መሠረት ማድረግ ይገባዋል። አንደኛው እና ዋነኛው ተግባር ህጋዊ ተግባር (Legal function) ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ስታትስቲካዊ ተግባር (Statistical function) ነው። የሁለቱ ተግባራት ጣምራ የአተገባበር መሠረት ደግሞ የሕዝብ ክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ነው። የሕዝብ የክብር መዝገብ ምዝገባ ስርዓትና የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ሥርዓት መሠረታዊ ልዩነትና አንድነታቸውን ለይቶ መገንዘብ ሥርዓቶቹ ሊከተሉ የሚገባቸውን የቴክኒክ፣ የአስተዳደርና የህግ አደረጃጀትና መዋቅራዊ አዘረጋግ ስልትን በብቃት ለመንደፍ ያስችላል። ጠለቅ ተደርጎ ሲታይ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃዎች የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ተረፈ ምርቶች (by-products) ናቸው። ይኸም ማለት ቀጣይ፣ ቋሚ፣ በሽፋኑና በጥራቱ የተሙዋላ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃ ለማግኘት የምዝገባ ሥርዓቱ በተሟዋላ አኳኋን መቋቋም ይኖርበታል።

የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ በዋነኝነት ግለሰባዊ የህግና የስታትስቲክስ መረጃዎችን በያዙ የመረጃ መሰብሰቢያ መዝገቦችና የስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጾች ይደራጃል። በኢትዮጵያ የሕዝብ የክብር መዝገብ መዝገቦች በአራት የወሳኝ ኩነት ዓይነቶች ላይ በመመሥረት በተዘጋጁ የምዝገባ መዝገቦች ተከፍለው ይደራጃሉ። እነርሱም የልደት የሕዝብ የክብር መዝገብ፣ የሞት የህዝብ የክብር መዝገብ፣ የጋብቻ የህዝብ የክብር መዝገብ እና የፍቺ የሕዝብ የክብር መዝገብ ናቸው። በተመሳሳይ የወሳኝ ኩነት ስታቲስቲክስ መረጃዎችን ለማጠናቀር የሚያስችሉ በአራት ወሳኝ ኩነቶች ላይ የተመሠረቱ የወሳኝ ኩነት ስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጾች ይደራጃሉ። እነርሱም የልደት ስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጽ፣ የሞት ስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጽ፣ የጋብቻ ስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጽ፣ እና የፍቺ ስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጽ ናቸው። በተለይም በወሳኝ ኩነት መዝገቦች ውስጥ የሚካተቱ የመረጃ

ዓይነቶችና የአመዘጋገብ ሥርዓታቸው ዓለም አቀፍ መርህን መሠረት አድርገውና የሀገሪቱን የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ስነ-ህዝባዊና አስተዳደራዊ አወቃቀርና አደረጃጀት አጣምረው በጥናትና ምርምር ላይ ተመሥርተው በተዘጋጁ የቴክኒክ መመሪያዎችና በምዝገባ ህጉ በመደገፍ ይደራጃሉ። ለመዝገቦቹ መረጃ አሰባሰብ አፈፃፀም ሀገራዊ ይዘት ያለው የምዝገባ ህግ አስፈላጊ በመሆኑ መንግስት በተዘጋጀው ቴክኒካዊ የአመዘጋገብ መመሪያ መሠረት ለመፈፀም የሚያስችልና ከሀገሪቱ የህግና የአስተዳደር አወቃቀር እንዲሁም የስታትስቲክስ ስርዓት ጋር የሚጣጣም የምዝገባ ህግ ማውጣት ይገባዋል።

በበርካታ የዓለማችን ክፍል እንደታየው ሁሉ የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓትን በኢትዮጵያ ማቋቋም ረጅም የዝግጅት ጊዜን ይጠይቃል። በቅድሚያ ዓለም አቀፍ የምዝገባ መርሆዎችን እና የተለያዩ ሀገሮችን የምዝገባ ተሞክሮ መነሻ ያደረገና ከሀገሪቱ ተጨባጭ የህግ፣ የአስተዳደርና የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት አሰጣጥ አሠራሮች ጋር የተገናዘበ የምዝገባ አሠራር መመሪያና ህግ መቅረጽ ያስፈልጋል። ይኸ ዝግጅት በአመዛኙ በንድፈ ሀሳብ ደረጃ የሚቀርብ ሲሆን ይኸንንም የንድፈ ሃሳብ ዝግጅት በመስክ ላይ መፈተሽና በተግባር ፍተሻው ከተገኘው ተሞክሮም ንደፈ ሃሳቡን ደረጃ በደረጃ ማሻሻልና ማዳበር ይጠይቃል። ይኸም የንድፈ ሀሳብ ዝግጅትና በተግባር የመፈተሽ ሥራ ራሱን በቻለ የምዝገባ ሥርዓቱ አደራጅ ተቋም መካሄድና በተደጋጋሚ በሚካሄዱ ሙከራዎች መፈተሽ አለበት።

በዚህም ሂደት በዋነኝነት፡-

- በሀገሪቱ የመንግስት አስተዳደር አደረጃጀት ላይ በመመሥረትና ከህግ አውጪው፣ ከህግ አስፈፃሚውና ተርጓሚው አስተዳደራዊ አደረጃጀትና የአሠራር ስርዓት ጋር በማገናዘብ የምዝገባ ሥርዓቱ አስተዳደራዊና ድርጅታዊ አወቃቀር ምን ሊመስል እንደሚገባ የሚያመለክት ጥናታዊ መመሪያ ማዘጋጀት፣

- ከሀገር አቀፍ የስታትስቲክስ መረጃ አቅርቦትና አጠቃቀም አስተዳደራዊና ድርጅታዊ አወቃቀር አንፃር የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ቴክኒካዊና አስተዳደራዊ አወቃቀር ምን መሆን እንደሚገባው የሚያመለክት ጥናታዊ መመሪያ ማዘጋጀት፣

- ከሀገር አቀፍ ጀምሮ እስከ ትንሹ የአስተዳደር ዕርከን አልፎም በግለሰብ ደረጃ የህግና የአስተዳደር እንዲሁም የልማት ዕቅዶች ዝግጅት፣ አተገባበርና አደረጃጀት እንዲሁም ግልጋሎት አሰጣጥ ከወሳኝ ኩነቶች ግለሰባዊና ጥቅል መረጃዎች አቅርቦትና አጠቃቀም አንፃር ምን ሊመስል እንደሚገባ የሚያመለክት ጥናታዊ መመሪያ ማዘጋጀትን ይጠይቃል።

በዚህ ረገድ የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓት የማቋቋም ዋና ዋና የተግባር ዘርፎችና የአፈፃፀም ስልቶች ከታች ተመልክቷል።

## 5.1 አጠቃላይ የዝግጅት ተግባራትና የአፈፃፀም ስልት

ተግባር ሀ፦ ሀገር አቀፍ የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የቴክኒክና የአስተዳደር አወቃቀርና አደረጃጀትን የተመለከተ ጥናትና ምርምር በማድረግ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የቴክኒክ መመሪያ ማዘጋጀት፣

አፈፃፀም - ይኸንን ተግባር ከሕዝብ የክብር መዝገብ መረጃ ማመንጨት፣ አቅርቦትና አጠቃቀም ጋር የተዛመደ ተግባርና ኃላፊነት ከተጣለባቸው የህግ፣ የአስተዳደርና የማህበራዊ አገልግሎት ዘርፎች እንዲሁም የስታትስቲክስ ተቋማት የተውጣጣ የመንግስት አካል እንዲያዘጋጀው ማድረግ፣

ተግባር ለ፦ ሀገር አቀፍ (ሞዴል) የምዝገባ ህግ ማዘጋጀት፣

አፈፃፀም - ይኸንን ተግባር ጉዳዩ በሚመለከተው የፍትህ ሚ/ር አስተባባሪነት (አሁን ባለው አደረጃጀት የማስተባበሩ ኃላፊነት የህግና የፍትህ ሥርዓት ምርምር ኢንስትትዩት ሊሆን ይችላል) የጤና፣ የስነ-ህዝብ ስታቲስቲክስ እና የአስተዳደር ተቋማትን በሚያሳትፍ መልኩ አንድ አካል በማደራጀት የምዝገባ ህጉ ረቂቅ እንዲቀረጽ ማድረግ፣

ተግባር ሐ፦ ሀገር አቀፍ የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ምዝገባ ሥርዓት ቴክኒካዊና አስተዳደራዊ አወቃቀርና አደረጃጀትን የተመለከተ ጥናትና ምርምር በማድረግ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃ አጠናቃቀር የቴክኒክ መመሪያ ማዘጋጀት፣

አፈፃፀም - ይኸንን ተግባር የስነ-ሕዝብ ስታቲስቲክስ መረጃዎችን የሚያጠናቅረው የስታትስቲክስ መ/ቤት ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸውን (በተለይም የጤና ጥበቃ ሚ/ር) አካላት በማካተት እንዲያዘጋጀው ማድረግ፣

ተግባር መ፦ በሀገሪቱ የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ እና ስታትስቲክስ ሥርዓቶችን በማቋቋምና በማደራጀት እንዲሁም በቀጣይነትና በቋሚነት በበላይነት በመቆጣጠር፣ በማስተባበርና ተግባሩን በማከናወን ኃላፊነቱን የሚወስደውን የመንግስት ተቋም መሰየም ወይም ማቋቋም፣

አፈፃፀም - ይኸንን ተግባር ለማከናወን ሥልጣንና ኃላፊነቱ ሊሰጣቸው የሚችሉ ነባር ተቋማት ሊኖሩ ይችላሉ፤ ወይንም ደግሞ እንደ አዲስ ሊቋቋሙ ይችላሉ። ይኸም ሲሆን የምዝገባውን እና የስታትስቲክሱን ተግባራት ለማከናወን ከተግባርና ኃላፊነት፣ ከሙያ፣ ከአደረጃጀት፣ ከመንግስት አስተዳደር አወቃቀር፣... አንፃር ተጠንቶና የተቋማቱን ምንነት፣ ማንነትና አወቃቀር በሚገልጽ አኳኋን በጥናታዊ ዶክመንት ተደግፎ መቅረብ ይኖርበታል።

ተግባር ሠ፡- የቴክኒክ መመሪያዎችን መርምሮ የሚያፀድቅ ብሄራዊ የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ አማካሪ ኮሚቴ ማቋቋም፤

አፈፃፀም - ለብሄራዊ አማካሪ ኮሚቴው ሥራ አመቺ እንዲሆን ከየሙያ ዘርፎች የተውጣጡ ባለሙያዎችን ያካተቱ የቴክኒክ አማካሪ ኮሚቴዎችን ማቋቋም፤

ለምሳሌ፡-

- የህግ አማካሪ የቴክኒክ ኮሚቴ
- የማህበራዊና ኢኮኖሚ አገልግሎት ሰጪ የሥራ ዘርፎች የቴክኒክ አማካሪ ኮሚቴ
- የስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ የቴክኒክ አማካሪ ኮሚቴ

ተግባር ረ፡- የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ እና ስታትስቲክስ ሥርዓቶችን ያጣመረ አንድ ወጥ የቴክኒክ እና የአስተዳደር አወቃቀርና አደረጃጀት መመሪያ ከላይ የተጠቀሱትን መመሪያዎች በማጣመር ማዘጋጀት፤

አፈፃፀም - ይኸንን ተግባር የሕዝብ የክብር መዝገብ ምዝገባ ሥርዓቱንና የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ሥርዓቱን በቴክኒክ እና በአስተዳደር አቀናጅቶ የሚቆጣጠረውና የሚመራው አካል እንዲያዘጋጅ ማድረግ፤

ተግባር ሰ፡- ሀገር አቀፍ የድርጊት ፕሮግራም መቅረጽ፤

አፈፃፀም - ይኸንን ተግባር በሀገር አቀፍ ደረጃ የምዝገባውን እና የስታቲስቲክሱን ተግባራት የሚቆጣጠረው፣ የሚያስተባብረውና የሚመራው የማዕከል አካል እንዲያዘጋጀው ማድረግ፤

ተግባር ሸ፡- ሀገር አቀፍ የትምህርትና ቅስቀሳ መመሪያ ማዘጋጀት፣

አፈፃፀም - ይኸንን ተግባር በሀገር አቀፍ ደረጃ የምዝገባውን እና የስታቲስቲክሱን ተግባራት የሚቆጣጠረው፣ የሚያስተባብረውና የሚመራው የማዕከል አካል እንዲያዘጋጀው ማድረግ፣

ተግባር ቀ፡- ሀገር አቀፍ የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ በጀት ማዘጋጀት፣

አፈፃፀም - ይኸንን ተግባር በሀገር አቀፍ ደረጃ የምዝገባውን እና የስታቲስቲክሱን ተግባራት የሚቆጣጠረው፣ የሚያስተባብረውና የሚመራው የማዕከል አካል እንዲያዘጋጀው ማድረግ፣

ተግባር በ፡- ሀገር አቀፍ የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓት መረጃ ውጤቶች የአጠቃቀም ሥርዓት የቴክኒክ መመሪያ ማዘጋጀት፣

አፈፃፀም - ይኸንን ተግባር በሀገር አቀፍ ደረጃ የምዝገባውን እና የስታቲስቲክሱን ተግባራት የሚቆጣጠረው፣ የሚያስተባብረውና የሚመራው የማዕከል አካል እንዲያዘጋጀው ማድረግ፣

## 5.2 የሙከራ ጥናት

ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው በማናቸውም መልኩ ሊሰበሰብ ለታቀደ መረጃ የተዘጋጁ የንድፈ ሃሳብ የመረጃ መሰብሰቢያ መመሪያዎችና መጠይቆች በዋናው ሥራ ላይ ከመዋላቸው አስቀድሞ መሞከር አለባቸው። ይኸም ማለት የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ መዝገቦች፣ የወሳኝ ኩነት ስታትስቲክስ መሰብሰቢያ ቅጾችም ሆኑ ልዩ ልዩ መመሪያዎች ለዋናው ሥራ ከመዋላቸው አስቀድሞ በተለይ በመስክ መሞከር አለባቸው። በመሆኑም ከምዝገባ ሥርዓቱ የዝግጅት ተግባራት አንዱና ዋነኛው ሥራ የሙከራ ጥናት ማድረግ ነው። በሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓት ማቋቋም ሁለት ዕርከን ያለው የሙከራ ጥናት እንደሚካሄድ ይጠበቃል። እነርሱም ሀገር አቀፍ ቅደመ-ሙከራ ጥናትና ክልል አቀፍ ሙከራ ጥናት በመባል ተከፍለዋል። በአጠቃላይ አገላለጽ የሙከራ ጥናቶቹ በሚከተሉት ተግባራት ላይ በመመርኮዝ ይካሄዳሉ።

⇒ የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ የአመዘጋገብ መመሪያ ዝግጅትና የመስክ ፍተሻ፣

⇒ የምዝገባና የስታቲስቲክስ መረጃ መሰብሰብ ተግባራትን ለማከናወን የህግ ድጋፍ ለማግኘት ቀደም ሲል የወጡ ህጎችን በመመርመር ለሙከራው ሥራ

የሚያገለግል የምዝገባ አሠራር መመሪያ ማዘጋጀት (በተለይ ለሀገር አቀፍ ቅድመ ሙከራ ጥናት የምዝገባ ህጉ ገና ሥራ ላይ ያልዋለ ከሆነ፣

⇒ የወሳኝ ኩነቶች የምዝገባ ህግ ረቂቅ ዝግጅትና የመስክ ፍተሻ፣

⇒ የወሳኝ ኩነቶች የምዝገባና ስታቲስቲክስ የዕቅድና አፈፃፀም ስልት ረቂቅ ዝግጅትና የመስክ ፍተሻ፣

⇒ የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የአስተዳደር አደረጃጀትን የሚያሳይ ድርጅታዊ መዋቅር፣ ተግባርና ኃላፊነት ዝግጅትና የመስክ ፍተሻ፣

⇒ የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ መረጃ ቅንብር እና መረጃ አጠቃቀም ድርጅታዊ አወቃቀርና ቴክኒካዊ አፈፃፀም መመሪያ ዝግጅትና የመስክ ፍተሻ፣

⇒ ከወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና የስታቲስቲክስ ሥርዓት የዕቅድና አፈፃፀም ስልት ጋር ተያይዞ በቀረበው መርሀ ግብር ላይ በመመሥረት የሙከራ የምዝገባና የስታትስቲክስ መረጃ መሰብሰብ የሥራ ሂደትን ማካሄድ፣

## 5.2.1 የሀገር አቀፍ ቅድመ ሙከራ ጥናት ተግባራት

- የሕዝብ የክብር መዝገቦች ቅርጽና ይዘትን መመርመርና መፈተሽ፣
- የህዝብ የክብር መዝገቦች መረጃ አመዘጋገብ መመሪያን መፈተሽና ማዳበር፣
- የህዝብ የክብር መዝገቦች መረጃ አመዘጋገብ፣ የምስክር ወረቀቶች ዝግጅትና አሰጣጥ አሠራሮችን መፈተሽ፣
- የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አስተዳደራዊና መዋቅራዊ አደረጃጀቱን መፈተሽ፣
- የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጾችን ቅርጽና ይዘት መመርመርና መፈተሽ፣
- የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጾች መረጃ አመዘጋገብ፣ አስተዳደራዊና መዋቅራዊ አደረጃጀቱን መፈተሽ፣
- የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ህግ ረቂቅን መፈተሽ፣
- የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓት የዕቅድ አፈፃፀም ስልትና መርሀ ግብርን መፈተሽ፣
- የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጾች መረጃን የኮምፒዩተር ቅንብር አደረጃጀት መፈተሽ፣
- በሕዝብ የክብር መዝገብ መረጃ አመዘጋገብ የኩነት መከሰት ጠቋሚና

አስመዝጋቢ ተቋማትንና ግለሰቦችን በሚመለከት የተዘጋጁ ቅጾችና መመሪያዎችን ብቃት መፈተሽ፣

- በሕዝብ የክብር መዝገብ መረጃ ምዝገባ አፈፃፀም የቀበሌ የሕዝብ የክብር መዝገብ ዋና ክፍሎችን አደረጃጀትና የሥራ አፈፃፀም መፈተሽና መገምገም፣

## 5.2.2 የክልል ሙከራ ጥናት ተግባራት

### ሀ. የዝግጅት ተግባራት

⇒ የክልል/ሎች የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የአስተዳደርና የኦፕሬሽን መዋቅሮችን መዘርጋት፣

⇒ የሕዝብ የክብር መዝገብ ምዝገባ እና የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥራን የሚያከናውኑ የመንግሥት ተቋማት ለዋናው ሥራ በተዘጋጀው መርሀ ግብር መሠረት መዋቅራቸው ተዘርግቶ የሙከራውን ሥራ እንዲያከናውኑ አስፈላጊውን ህጋዊ፣ አስተዳደራዊና ቴክኒካዊ ዝግጅት ማጠናቀቅ፣

⇒ በቅድመ-ሙከራ የተፈተሹ የምዝገባ መዝገቦችና የስታቲስቲክስ ቅጾች እንዲሁም ልዩ ልዩ የጠቋሚ እና የአስመዝጋቢ ቅጾችን የመጨረሻ ቅርጽና ይዘት መስጠት፣

⇒ በቅድመ-ሙከራ የተፈተሹ የምዝገባ እና የስታቲስቲክስ መረጃ አመዘጋገብ መመሪያዎችን የመጨረሻ ቅርጽና ይዘት መስጠት፣

⇒ በማዕከል በሞዴልነት የተዘጋጀውን የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ረቂቅ ህግ ለሙከራ ተግባር ለማዋል እንዲቻል በክልሉ/ሎች የህግ ዕውቅና እንዲያገኝ ማድረግ፣

⇒ ለምዝገባ ክልል/ሎች የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ ለህብረተሰቡ፣ ለአገልግሎት ሰጪ ተቋማት በቀጣይነትና በቋሚነት ለማካሄድ አስፈላጊ ዝግጅቶችን ማጠናቀቅ፣

⇒ የህግ፣ የማህበራዊ እና አስተዳደራዊ ግልጋሎት ሰጪ ተቋማት ከምዝገባ ሥርዓቱ የሚገኙ መረጃዎችን በመጠቀም እንዲሁም ህብረተሰቡ በመረጃነት ለልዩ ልዩ ጉዳዮች ሲያቀርብ በምን ሁኔታ ማስተናገድ እንደሚገባቸው፣ ለዚህም ዝግጅት እንዲያደርጉ ማድረግ፣

⇒ የሕዝብ የክብር መዝገብ ዋና ክፍሎችን በክልሎች በየቀበሌው አስተዳደር መዋቅር ሥር ማቋቋም፣

⇒ የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹሞችን መሰየም፣

## ለ. የመስክ ሥራ

⇒ በማዕከል በተዘጋጀው የሕዝብ የክብር መዝገብ አመዘጋገብ የቴክኒክ መመሪያና በምዝገባ ህጉ በመመሪት የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ምዝገባዎችን ማካሄድ፣

⇒ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና የፍቺ ምስክር ወረቀቶችን በማዘጋጀት ለባለጉዳዮች መስጠት፤

⇒ በልደት፣ በሞት፣ በጋብቻና ፍቺ ስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጾች የኩነቶች መረጃዎችን በመሙላት ወደሚመለከታቸው የስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤቶች መላክ፤

## ሐ. የመረጃ ጥንቅርና ቅንብር እንዲሁም ሥርጭት ሥራ

⇒ ግለሰባዊ የኩነት መረጃዎችን ለህዝብ ጤና አጠባበቅ እና ልዩ ልዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች ሊሰጡ በሚችሉበት አኳኋን በማጠናቀር የምዝገባ ህጉ በሚፈቅደው መሠረት ዝርዝር መረጃዎችን ለተጠቃሚዎች መስጠት፤

⇒ የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ መረጃዎችን በማዕከል በማጠናቀርና በመተንተን በየአስተዳደር ዕርከን ደረጃው የወሳኝ ኩነት ስታቲስቲክስ መረጃዎችን በሪፖርት መልክ እያዘጋጁ ማሰራጨት፤

## 5.3 ሀገር አቀፍ ቅድመ - ሙከራ ጥናት ተግባራት የአፈፃፀም ስልት

⇒ በቅድመ ሙከራ ጥናት ወቅት እንዲከናወኑ የተዘረዘሩት ተግባራት በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለስልጣን (አሁን እየተደራጀ ባለው የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት በኩል) ሊከናወኑ የሚችሉ ተግባራት ናቸው። ይኸም ሲሆን የሚከተሉት ተጓዳኝ አደረጃጀቶች መፈጠር ይገባቸዋል።

- ሀገር አቀፍ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሙከራ ጥናት አስተባባሪ ከፍተኛ የቴክኒክ ኮሚቴ ማቋቋም፣ ተግባርና ኃላፊነቱን እንዲሁም አባላቱን መሰየም፤
- የኮሚቴው አባላት ስብጥር ከሚከተሉት ተቋማት የሚውጣጡ ከፍተኛ ኤክስፐርቶች ይሆናሉ።

    1. ከፍትህ ሚ/ር
    2. ከሕግና ፍትህ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲተዩት
    3. ከጠቅላይ ፍርድ ቤት

4. ከጤና ጥበቃ ሚ/ር
5. ከአ.አ ማዘጋጃ ቤት
6. ከስነ-ህዝብ ጽ/ቤት
7. ከከተሞች ፕላን ኢንስቲትዩት
8. ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለስልጣን

⇒ሙከራው በሚካሄድባቸው የተመረጡ የቀበሌ አስተዳደሮች የሕዝብ የክብር መዝገብ ምዝገባ ዋና ክፍሎችን በተዘጋጀው አወቃቀር መሠረት ማደራጀት፣ ተገቢውን የሰው ኃይል መመደብ፣ (በሙከራው ወቅት ለቀበሌው ከሚመደበው የማዕከል ቅጥር መዝጋቢ ጋር አብረው የሚሠሩ ናቸው)

⇒ሙከራው በሚካሄድባቸው የተመረጡ የቀበሌ አስተዳደሮች በምዝገባው አወቃቀር መሠረት የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹም መሰየም፣

## 5.4 *የክልል ሙከራ ጥናት ተግባራት የአፈፃፀም ስልት*

⇒በሙከራ ጥናት ወቅት እንዲከናወኑ የተዘረዘሩት ተግባራት በማዕከል የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ እና የስታትስቲክስ ተግባራትን እንዲቆጣጠር፣ እንዲያስተባብርና እንዲመራ ስልጣን የተሰጠው(ጣቸው) ተቋም(ማት) ምዝገባውን በክልል ለማከናወን ኃላፊነት ከተሰጣቸው የክልል ተቋማት ጋር እንዲያካሂዳቸው(ዷቸው) ማድረግ ያስፈልጋል። ይኸም ሲሆን የሚከተሉት የዝግጅት ተግባራት አስቀድመው መጠናቀቅ አለባቸው።

- በተዘጋጁት እና በፀደቁት የቴክኒክ መመሪያዎች ላይ በመመርኮዝ የምዝገባውን እና የስታቲስቲክስ ተግባራት ፈፃሚ ተቋማት በድርጅታዊ፣ አስተዳደራዊና ቴክኒካዊ አቋማቸው ተደራጅተው መገኘት፣
- የምዝገባ ህጉ ሙከራ ለሚካሄድባቸው ክልል/ሎች ተፈፃሚ ለማድረግ የሚያስችሉ አደረጃጀቶችን ማጠናቀቅ፣
- የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹሞች መሰየም፣
- ለሕዝብ የክብር መዝገብ ምዝገባ አፈፃፀም አስፈላጊ ተጓዳኝ ተግባራት በመባል የተለዩትን መፈፀም፣ (ለምሳሌ በቀበሌ የቤቶችን የቤት ቁጥር አሰጣጥን፣ የመንግስት የህግና የአስተዳደር ልዩ ልዩ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን የአስተዳደር መዝገብ አያያዝ አሠራርን በአግባቡ እንዲያቋቁሙ ማድረግ፣ የመራጮች መዝገብ አያያዝና የሰብዓዊ መብት ጥበቃ ተቋማት ከምዝገባ ሥርዓቱ የሚመነ ግለሰባዊ

መረጃዎችን ለመጠቀም ተገቢውን አደረጃጀት እንዲያዙ ማድረግ፣ ...ወዘተ)

- ለሙከራው ጥናት በመንግስት በኩል በቋሚነት የተመደበውን በጀትና መርሀ ግብር በየጊዜው እየመረመሩ ዕድሳት ለማድረግ የሚያስችል አደረጃጀት መፍጠር፣

⇒ በማዕከል በተዘጋጀው የትምህርትና ቅስቀሳ መመሪያ መሠረት ሙከራ ጥናቱ በሚካሄድባቸው ክልሎች ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ፣

⇒ የሙከራ ጥናቱን ሂደት በተለያዩ መድረኮች ለምሳሌ ወርክሾፖች፣ ሴሚናሮች፣... ወዘተ ለመንግስት ፖሊሲ አውጪዎች፣ ህግ አስፈፃሚዎች፣ ተርጓሚዎችና ግልጋሎት ሰጪ ተቋማት፣ ለትምህርትና ጥናት ተቋማት፣ ለሙያ ማህበራት... ወዘተ ማሳወቅ፣

## 6. ተጓዳኝ የጥናትና ምርምር የዝግጅት ተግባራት

የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ስርዓትንም ሆነ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ሥርዓትን በታዳጊ ሀገሮች ለመመሥረት የተደረገው ጥረት ብዙም የተሳካ አይደለም። አሁንም ቢሆን እነዚህ ስርዓቶች ተሟልተው የሚገኙት በኢኮኖሚ በበለፀጉ አገሮች ነው። እንደ ኢትዮጵያ ባሉ በቁጥር ከሚጠቀሱ ሀገሮች በስተቀር በሌላው ዓለም ጊዜው ይለያይ እንጂ እነዚህን የመረጃ ስርዓቶች ለመመሥረት ተደጋጋሚ ሙከራዎች ባልተቋረጠ መልኩ እየተካሄዱ ይገኛል። ይኸም ሲሆን በኢትዮጵያ ቢያንስ የምዝገባ ህጉን ዕውቅና መስጠት እንኳ አልተቻለም። ሥርዓቶቹ በዓለማችን ካሳለፉት ረጅም ዕድሜ አንፃር በቴክኒካዊ አሠራራቸው፣ በድርጅታዊ አወቃቀራቸው፣ በመረጃ ግብዓትነታቸውና ከዚህም ጋር ተያይዞ በመጣው የመረጃ አጠነቃቀር ቴክኖሎጂ ዕድገታቸው ከፍተኛ ለውጥና ዕድገትን አሳይተዋል። በመሆኑም የተለያዩ ሀገሮች ልምዶችን እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ገና ጀማሪ ሀገሮች ለመጠቀም ሲታሰብ የየሀገሮችን ሙሉ ተሞክሮ መመርመርና ከዛሬው ዘመን ጋር ተቀናጅተው በጥንቃቄ መታየት የሚችሉበትን አሠራር መፍጠር ይጠይቃል። በዚህ ረገድ የሥርዓቶቹን ጥምረት መሠረት ያደረገ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ መረጃ አሰባሰብ፣ አጠነቃቀርና አጠቃቀም እንዲሁም አስተዳደራዊና ድርጅታዊ አወቃቀር በሀገሪቱ ለመዘርጋት የሚያስችል የአሠራር መመሪያ ለማዘጋጀት ጥናትና ምርምር የሚያደርግ ራሱን የቻለ ቋሚ «የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ጥናትና ምርምር ማዕከል» የጥናትና ምርምር ማዕከል ማቋቋም ይጠይቃል። ይኸ የጥናትና ምርምር ማዕከል ሥርዓቶቹ በተሟላ ሁኔታ ከሚገኙባቸው ሀገሮች ልምድ፣ በኢኮኖሚ ኋላ ቀር ሀገሮች ሥርዓቶቹን የተለያዩ ቴክኒካዊ አማራጭ አሠራሮችን በመንደፍ በተሟላ አኳኋን ለማቋቋም እያደረጉ ያሉትን ሙከራዎችና የተገኙ ውጤቶችን ከሀገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማጣመር የሚያጠና ተቋም ሊሆን ይገባል።

በዚህ የጥናትና ምርምር ተቋም አደረጃጀት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት (ዩኒቨርስቲዎችና ኮሌጆች) በተለይም የህግ፣ የስነ-ሕዝብ ስታትስቲክስና የሕዝብ አስተዳደር እንዲሁም የጤና የትምህርት ዘርፎች በምርምሩና በመማር ማስተማሩ ተግባር የምዝገባውን አሠራር አዋህደው በማስጎዝ ረገድ ሰፊ ድርሻ ሊኖራቸው በሚችልበት መልኩ ሊሳተፉ ይገባል። በተመሳሳይ የጥናትና የምርምር ተቋሙ በተለይ የህግ ተርጓሚ ተቋማት፣ የስታትስቲክስ መ/ቤት፣ የህዝብ አስተዳደር መ/ቤቶች እንዲሁም የጤናና የትምህርት ሚኒስቴር መ/ቤቶች አልፎም ከላይ የተጠቀሱት የሙያ ዘርፎች የሙያ ማህበራት በባለቤትነትና በተሳታፊነት ሊሠሩ በሚችሉበት አኳኋን ሊደራጁ ይገባል።

በመሠረቱ ከሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ስርዓት የሚገኙ ግለሰባዊ መረጃዎች ዋነኛ ጥቅም የግለሰቦችን ህጋዊ ማንነት በህግ ጉዳዮች፣ በአስተዳደርና ልዩ ልዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግልጋሎቶችን በመስጠትና በመቀበል በመረጃነት የሚያገለግሉ ህጋዊ መረጃዎችን ለግለሰቦችና ለአስፈፃሚ የመንግስት መ/ቤቶች እንዲሁም የግል ተቋማት ማስገኘት ነው። ከምዝገባ ስርዓቱ የሚገኙ መረጃዎችን በአግባቡና በተቀላጠፈ መንገድ ጥቅም ላይ ለማዋል በተለይ የመንግስት የህግ፣ የአስተዳደርና ማህበራዊ ግልጋሎት ሰጪ ተቋማት የውስጥ አደረጃጀታቸውንና አሠራራቸውን ለመረጃ አሰጣጥና አጠቃቀም አመቺ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ለዚህም አንዱና ዋነኛው መሠረት በአስተዳደር መዛግብት መረጃ አያያዝ፣ አጠነቃቀርና አጠቃቀም ብቃታቸውን ማሳደግ ነው። ይኸ የመረጃ አሰባሰብ፣ አጠነቃቀርና አጠቃቀም ዘርፍ አደረጃጀቱና አተገባበሩ በተለይም በታዳጊው ዓለም ብዙ ትኩረት ያልተሰጠውና በጥናት ላይ ተመሥርቶ በቴክኒካዊ መመሪያዎች ዝግጅት የተደረገበት አይደለም። በመሆኑም የአስተዳደር መዛግብት መረጃ አያያዝ፣ አጠነቃቀርና አጠቃቀም አሠራርን ማሳደግ አንዱና ዋነኛው የምዝገባው ተጓዳኝ የሥራ ዘርፍ ሊሆን ይገባል።

በተመሳሳይ የስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ መረጃዎችን የሚሰበስበውና የሚያጠናቅረው የስታትስቲክስ መ/ቤት ኩነቶች በተከሰቱበት ወቅት ከተያዙ ግለሰባዊ መረጃዎች ላይ መሰብሰብ የሚገባቸውን ወሳኝ የስነ-ህዝብ መረጃዎችን (ለምሳሌ - ዕድሜ፣ የተወለዱ ልጆች ማንነት፣ የሞቱ ሰዎች ማንነትና ባህርያት፣ የጋብቻና ይቺ መረጃዎች፣ ...ወዘተ) የሕዝብ ቆጠራና መሰል ናሙና ጥናቶችን ሲያካሄድ በሕዝብ የክብር መዝገብ ምዝገባ ስርዓት አማካይነት ከተገኙ ትክክለኛና ወቅታዊ ግለሰባዊ ሰነዶች ላይ በመመሥረት ለመሰብሰብ ወደሚያስችለው መረጃ አሰባሰብ አሠራር ማቃናት ይገባዋል። በመሆኑም የስታትስቲክስ መ/ቤቱ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃዎችን ከማጠናቀር ፍላጎት ባሻገር ዘላቂና ጥራት ያለው የሥነ-ህዝብ ስታትስቲክስ መረጃዎችን በቆጠራዎችና ናሙና ጥናቶች ለመሰብሰብ ትክክለኛ ግለሰባዊ የግብዓት መረጃዎችን ለማግኘት የሚያስችለውን የምዝገባ ስርዓት በአገር አቀፍ ደረጃ እንዲቋቋም በማድረጉ የበኩሉን ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል።

ከዚህም ሌላ በቆጠራና መሰል የናሙና ጥናቶች የሚገኙ መረጃዎች በጥናቱ ወቅት ያለውን ሁኔታ የሚያመለክቱ በመሆናቸው መረጃዎቹን ቀጣይ ለማድረግ ተከታታይና ቋሚ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ምጣኔዎችን የሚያስገኘውን የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ሥርዓት ለማቋቋም የስታትስቲክስ መ/ቤቱ ይኸንኑ ፍላጎቱን ለሚመለከተው የመንግስት አካል በጥናት ላይ የተመሠረቱ ጽሁፎችን በማስደገፍ ማሳወቅና ማቅረብ ይጠበቅበታል። ከዚህም በላይ በተለይም በቆጠራዎች መሃከል የሚፈለግን ወቅታዊና ትክክለኛ የሥነ-ህዝብ ስታቲስቲክስ መረጃ እስከ ትንሹ የአስተዳደር ዕርከን ለማስገኘት የምዝገባ ሥርዓቱን አስፈላጊነትና የመቋቋሙን ጠቀሜታ ከተግባርና ሃላፊነቱ አንፃር ማሳወቅና ተገቢው አደረጃጀት እንዲፈጠር ማድረግ ይገባዋል።

# አባሪ ሀ

## በኢትዮጵያ የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓት ማቋቋም- ሀገር አቀፍ የድርጊት ፕሮግራም

### ማጠቃለያ

| ተ.ቁ | የፕሮግራሙ ዓይነት | የሚያከናውነው አካል | | | | | | የሚከናወንበት ጊዜ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በማዕከል | | የቴክኒክ አማካሪ ኮሚቴ | በክልል | | | |
| | | ምዝገባ | ስታትስቲክስ | | ምዝገባ | ስታቲስቲክስ | በቀበሌ | |
| 1 | ሀገር አቀፍ ቅድመ-ሙከራ ጥናት | ማስባ | ማስባ | ግብረ-ኃይል | - | - | ማስባ/መስተዳድር | 1994-1995 |
| 2 | በክልል «ሀ» ሙከራ ጥናት | የሕዝብ የክብር መዝገብ ምዝገባና ስታቲስቲክስ አስተባባሪ ኮሚቴ | ማስባ | ፌዴራል* + ክልል** | ፍትህ ቢሮ | - | መስተዳድር | 1996 |
| 3 | በክልል «ሀ» የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥራ እና በክልል «ለ» የሙከራ ጥናት | ኮሚቴ*** | ማስባ | ፌዴራል* + ክልል** | ፍትህ ቢሮ | - | መስተዳድር | 1997- |
| | 3.1 በክልል «ሀ» የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥራ | ኮሚቴ*** | | | | | | |
| | 3.2 በክልል «ለ» የሙከራ ጥናት | ኮሚቴ*** | ማስባ | ፌዴራል* + ክልል** | ፍትህ ቢሮ | - | መስተዳድር | 1997- |
| 4 | በክልል«ሀ» እና «ለ» የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥራ እና በክልል«ሐ» እና «መ» የሙከራ ጥናት | ኮሚቴ*** | " | ፌዴራል* + ክልል** | ፍትህ ቢሮ | - | መስተዳድር | 1998- |
| | 4.1 በክልል «ሀ» የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥራ | ኮሚቴ*** | " | ፌዴራል* + ክልል** | ፍትህ ቢሮ | - | መስተዳድር | 1998- |
| | 4.2 በክልል«ለ» የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥራ | ኮሚቴ*** | " | ፌዴራል* + ክልል** | ፍትህ ቢሮ | - | መስተዳድር | 1998- |
| | 4.3 በክልል«ሐ» እና «መ» የሙከራ ጥናት | ኮሚቴ*** | " | ፌዴራል* + ክልል** | ፍትህ ቢሮ | - | መስተዳድር | 1998 |
| | . | . | . | . | . | . | . | . |
| | . | . | . | . | . | . | . | . |
| | . | . | . | . | . | . | . | . |
| | . | . | . | . | . | . | . | . |
| | . | . | . | . | . | . | . | . |
| | . | . | . | . | . | . | . | . |
| 11 | የ«መጨረሻው ክልል» የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥራ እና ሀገር አቀፍ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥራ | ኮሚቴ*** | " | ፌዴራል* + ክልል** | ፍትህ ቢሮ | - | መስተዳድር | |
| | 11.1 በ«መጨረሻው ክልል» የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥራ | ኮሚቴ*** | " | ፌዴራል* + ክልል** | ፍትህ ቢሮ | - | መስተዳድር | |
| | 11.2 ሀገር አቀፍ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥራ | ኮሚቴ*** | " | ፌዴራል* + ክልል** | ፍትህ ቢሮ | - | መስተዳድር | |

* አባላቱ ከማዕከል የፌዴራል፣ (ፍትህ ፣ ጤና ጥበቃ፣ ትምህርትና ከመስተዳድር) መ/ቤቶች የተውጣጡ ይሆናሉ::

